ፓኖራማ ቁ 87

የትዝብት አድማስ

የካቲት 27 ቀን 2002 ዓም

<u>የኢሕአፓ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ</u>

ኢትዮጵያ ሀገራችን በገለልተኝነትና በሠላም ፈላጊነት ላይ የተመሠረተ የውጭ ፖሊሲ መከተል እንደሚኖርባት ኢሕአፓ ያምናል ። በዚህ መሠረታዊ መርኀ ላይ በመመርኮዝም ብሔራዊ ጥቅሟን በመጠበቅና በማስጠበቅ በነፃነትና በሰላም ከዓለም ሀገሮች ጋር አብሮ ለመኖር ምኞቷ ይሆናል።በመሆኑም፥በተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና በአፍሪካ ኅብረት ማዕቀብ ከተጣለባቸው በስተቀር ከማንኛወም የዓለም ሀገሮችጋር በሰላም አብሮ በመኖር፥ በእኩልትና በጋራ ጥቅም መሠረት ግንኙነቷን ታካሂዳለች ፤ታጠናክራለች ። ይህ መሠረታዊ ፖሊሲዋም ከጎረቤት ሀገሮች ጋር የበለጠ በሰላምና በመተባበር አብሮ ለመኖር ያስችላታል ። ከዚህም በቀር ለፍትኅ ለዴሞክራሲ፥ ለነፃነትና ለሰብዓዊ መብቶች ለሚታገሉ ሕዝቦች ሁሉ የኢትዮጵያ ድጋፍ አይለያቸውም ። <u>ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ፥ የራሷን ብሔራዊ ጥቅም መጠበቅና የሌሎችንም ማክበር የውጭ ፖሊሲዋ የማዕዘን ዋልታ ሆኖ ይኖራል።</u> በራስ ነፃነትና ልዕልና ላይ ተመርኩዞ የሚተረጎም የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ማለት ለኢሕአፓ አዎንታዊ ገልልተኝነት ማለት ነው ። ይህም ማለት፥ ከማንኛውም የዓለም ነፃ ሀገሮች ጋር የሠላም ፥ የንግድ ፥ የባኅል ፤ የትምህርት ፥ የሳይንስና ቴክኒዮሎጂ ግንኙነትና ትብብር እያደረገች ብሔራዊ ጥቅሟን ሁሉ ለማስከበር የተቻላትን ሁሉ ትፈጽማለች ማለት ነው። ከማንም ጎራ ጋር ወገን ሳትለይ በነፃነቷ ከሁሉም ጋር ወዳጅነት ለመመስረት በምታደርገው እንቅስቃሴ ሁሉ ገደብ ሊኖርበት አይችልም ።ይህም ለነጻነቷ ዋስትና መረጋገጫ ከመሆኑም በላይ ፥ ለውጭ ዲፕሎማሲዋ እንቅስቃሴ ተዓማኒንትን ያተርፍለታል። ይህ ፖሊሲ በአሁኑ ወቅት ሰፍኖ ያለውን የወያኔን ተንበርካኪ መሪዎች ባህርይና ድርጊት በጽኑ የሚጻረርና የሚቃወም ነው ። ኢትዮጵያ ሀገራችን የማንም ሀገር ጥቅም አስጠባቂና ፖሊሲ አስፈፃሚ ሀገር እንድትሆን ኢሕአፓ በጭራሽ አይፈልግም፤አይፈቅድም ።

የማንኛውም ሀገር የውጭ ፖሊሲ የዚያው ሀገር የውስጥ ፖለቲካና አስተዳደር ቀጥታ ነፀብራቅ እንደመሆኑ ፥ የሀገራችን የውጭ ፖሊሲ በዓለም አቀፍ ደረጃ አክብሮትና ተቀባይነት እንዲያገኝ ከተፈለገ፥ ሀገራችን የውስጥ አስተዳደሯና ፖለቲካዋ በዴሞክራሲ ሥርዓት ላይ መመስረት ይኖርበታል ። በመሆኑም ኢትዮጵያ ዜጎቿን በዴሞክራሲ ሥርዓት

እንዲተዳደሩ ከማድረግ ሌላ አማራጭ ሊኖራት ይችልም ፡፡ የኢሕአፓ የዲሞክራሲዊ ሥርዓት ራዕይ፥ በወረቀት ላይ ብቻ ሰፍሮ የሚቀርና ለይስሙላ ተብሎ ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ የሚሆን የቧልት ዴሞክራሲ ሳይሆን ፥ሕዝብ ያለተጽዕኖ በቀጥታ የሚሳተፍበት አሳታፊ ዴሞክራሲ ማለት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዕለት ጉርሱ፥ለዓመት ልብሱና ለመጠለያው ከማሰብና ከመጨነቅ አልፎ ተርፎ፥ ስለ ጠቅላላለ ኑሮውና ሕይወቱ፥ ስለ መሠረታዊ ጎልውናው ፥ስለሀገሩ ሁለንተናዊ ጉዳይ፥ ስለነፃነቱና ታሪኩ ፥ ዕምነቱና ባኅሉ ፥ስለ ወደፊቱ ዕድሉና ራዕዩ፥ስለ ፖለቲካ ፥ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ህይወቱ፥ስለ ሚመሰረተው መንግሥትና ስለሚመርጣቸው መሪዎች ፥በነፃ ተወያይቶና ተሳትፎ የሚወስንበት የፖለቲካ መልከዐ ምድር ሊመቻችለት ይገባል፡፡ የሕዝብ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰምረው ፥ የዜጎች ሙሉ ተሳትፎ ሲኖር እንደሆነ ግልፅ ነው ፡፡ በመሆኑም ኢትዮጵያ በዴሞክራሲ ሥርዓት ላይ የተመሠረተ የውጭ ፖሊሲ መርሆ እንድትከተል ማድረግ ፥ ሀገራችን የሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ኅብረተስብ አባል እንደትሆን ያስችላታል፡፡ እስከዛሬ ድረስ ሀገራችን ዘወትር የውጭ ተመጽዋች ሆና የቆየችው፥ የተፈጥሮ ድሃ ሆና ሳይሆን፥ ወይም ደግሞ ዜጎቿ ሥራ የማይወዱና ታታሪ ባለመሆናቸው ሳይሆን፥አሳታፊ ዴሞክራሲ አግኝተው ኢኮኖሚያቸውን በመገንባት ከድኅነት ለመላቀቅ ባለመቻላቸው ነው ፡፡ ዛሬ የሀገሯን ኢኮኖሚና ባጀት በውጭ ርዳታ ላይ የመሠረተች ብቸኛ ሀገር ብትኖር ኢትዮጵያ መሆኗ ዓለም የአወቀው ፀሀይ የሞቀው ሆኗል፡፡ በየትኛው የዓለም ታሪክ በውጭ ርዳታ ብቻ ከድኅነት ተላቅቆ ራሱን የቻለ ሀገር አይገኝም፡ የአንድ ሀገር ሕዝብና መንግሥት እጅና ጓንት ሆነው በመቆም ሀገራቸውን ከችግር ለማውጣት የሚችሉት ፥ ዜጎቹ በዴሞክራሲ ሥርዓት የራሳቸውን መንግሥት ሲመሰርቱና መሪዎቻቸውንም ሲመርጡ ብቻ ነው ፡፡እስካሁን ድርስ የተለያየ ቀለምና ለምድ እያጠለቁ የተፈራረቁት የሀገራችን አምባገነን መሪዎች ፥ከአንድ ጽንፍ ወደ ሌላው ጽንፍ እየተወራጩ የየራሳቸውን የሥልጣን ዕድሜ በማራዘም፥ የጭቆና አገዛዛቸውን በሕዝቡ ላይ ከመጫን በቀር ለታሪክ የሚሆን መልካም ትዝታን አላስመዘገቡም ፡፡ይህ በበኩሉ የሀገራችንን የውጭ ፖሊሲ ዘወትር የምዕራባውያን ተጠማኝና ደጀጠኝ አድርጎት ኖሯል ፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃዋ ኢትዮጵያ ነፃ የውጭ ፖሊሲዋን የምትመራበትን ቀን በናፍቆት የሚጠብቀውም በዚህ ምክንያት ነው ፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያ ልክ እንደሌሎቹ በልማት ወደኋላ የቀሩ ሀገሮች ሁሉ የውጭ ርዳታና ትብብር እንደሚያስፈልጋት የሚያከራክር አይደለም ፡፡ በተለይ በሳይንስና ቴክኒዮሎጂ ፥ ዕደ-ጥበብና መሃንዲስ፥ የቴክንክ ተግባራትና ትምህርት፥ ፋይናንስና የዕርሻ ዘዴ፥የመሳሰሉትን ዘመናዊ ርዳታ ማግኘት አለባት፡፡በገለልተኝነት ስም ብቻ በሯን ጠርቅማ ከዓልም ሥልጣኔ ተገልላ ልትኖር አትችልም ፡፡ ይህ ስለተባለ ግን ፣ በልማትና በርዳታ ሰበብ የሀገሪቱን ለም መሬት ለባዕድ አሳልፎ መስጠቱን ኢሕአፓ አጥብቆ ይቃወማል ፡፡ ኢትዮጵያዊ የሆነ መንግሥት፥የሀገሩን ለም መሬት ለባዕድ ሀገሮች መጠቀሚያ እንዲውል በሀራጅ ይሸጣል ተብሎ ይታሰባል ለማለት ባይቻልም ዛሬ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዐይኑ እያየ ጆሮው እየሰማ የመሃል አገሩ ለም መሬት ብቻ ሳይሆን፥ ዳር-ደንበሩም ጭምር ለባዕድና ለጉረቤት ሀገሮች እየተቸበቸበ ይገኛል፡፡ የሀገሩን ብሄራዊ ጥቅም በዚህ የከሃዲ ደረጃና ስፋት አሳልፎ የሚሰጥ ቡድን በሥልጣን ላይ ሲመጣ ማየት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የመጀመሪያው ጊዜ መሆኑ ቢያሳዝነውም ተስፋ ሳይቆርጥ ሁኔታውን በመለወጥ ነግ - ተነገ ወዲያ የሀገሩን ጥቅም እንደሚያስከብር ግን ማንም ዜጋ ሊጠራጠር አይችልም፡፡ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሀገሩን ብሔራዊ ጥቅምም ይሁን የራሱን ነፃነት የሚጠብቅለት ኢትዮጵያዊ መንግሥት እንደሌለው አምኖ የራሱን መንግሥት ለማምጣት እየታገለ ይገኛል ፡፡ የራሱን መንግሥት መስርቶም ሀገራዊ ነፃነቱንና ብሔራዊ ጥቅሙን እርሱ ራሱ ማስከበር እንደሚችል ያለፈ ታሪኩ ስለሚመሰክርለት ፥ በዚህ በኩል ጠላቶቹ ሁሉ ሊገነዘቡት ይገባል ፡፡

ለሀገራችን ኢትዮጵያ የምንመኝላት የተሟላ ነፃነትን ነው ስንል፥ ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማን ለማውለብለብና ፈንጠዝያን ለመግለጽ ብቻ ሳይሆን፥ በሁለንተናዊ ገጽታው ለሀገራችንና ለሕዝባችን በዘለቄታ መልኩ የሚጠቅም ነፃነት ማለታችን ነው፡፡ ይህ ምን ማለት ነው? የፖለቲካ ነፃነት ያለ ኢኮኖሚ ዕድገትና ጥንካሬ፥ያለ ዕርሻ ልማትና እንዱስትሪ መስፋፋት፥ ያለ ሳይንስና ቴክኒዮሎጂ ርምጃ በምንም ዓይነት ሀገራችን የተሟላ ነፃነት ይኖራታል ተብሎ አይታሰብም ማለት ነው ፡፡ ሀገራችን ከረሀብ ፥ ከበሽታ፥ ከመሀይምነት ፥ ከድኅነት፥ በጠቅላውላም ከኋላ ቀርነት እንድትላቀቅ ካስፈለገ፥ የእጆቿን የመዘርጋት አቅጣጫ መለወጥ አለባት፡፡ እጆቿን ለዕርዳታ ወደ ምዕራባውያን ከመዘርጋት ይልቅ፥ ወደ ሕዝቧ፤ ወደ መሬቷ፥ ወንዞቿና ወደ ከርሰ-ምድሯ ዘርግታ የራሷን አንጡራ ብሔራዊ ሀብቶች መጠቀም መቻል ይኖርባታል፡፡ ድልብ ሀብቷንና ወንዞቿን ለመጠቀም በምትሞክርበት ጊዜ የቅርብና የሩቅ ተቀናቃኞቿ እንቅፋት እንደሚሆኑባትም አስቀድመን ልንገነዘበው ይገባናል፡፡የፖለቲካ ነፃነታችንን አስከብረን ወድ ልማት አቅጣጫ በምናተኩርበት ወቅት ሊገጥመን የሚችለውን ማነኛውንም ዕንቅፋት ለማቋቋም አስፈላጊውን ጥንቃቄና ዝግጅት ማድረግ እንዳለብን፥ ብሔራዊ የሆነ ኢትዮጵያዊ መንግሥት ተቀዳሚ ተግባሩ ሊሆን ይገባል፡፡ በአሁኑ ወቅት ይህ ሊሆን አልቻለም፡፡ በእኛ ዕምነት ፥ሀገራችን ከአካባቢና ከሩቅ ጠላቶቿ ጥቃት ለመከላከልና የውስጥ ፀጥታዋንም አስከብራ ያለስጋት ወደ ልማቷ ለማተኮር ካስፈለጋት፥ሦስት ብሔራዊ ተቋማት ተጠናክረውና ተቀናጅተው በቅንብር እንዲሰሩ መደረግ አለባቸው ፡፡ እነርሱም የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት፥ የመከላከያ ኃይልና የኢንተሊጀንስ ድርጅት ናቸው ፡፡ በዓላማ ፥በተልዕኮና በይዘት የተለያዩ ተቋማት ሊመስሉ ቢችሉም ፥ የኢትዮጵያን ስትራተጂያዊ ጥቅምና ሀገራዊ ደህንነት በመጠበቅ በኩል አንድም ሦስትም መሆናቸው ታውቆ፥ በአስተማማኝ ደረጃ ተጣምረውና ተቀናጅተው የሚሰሩባት መንገድ ሊኖር ይገባል፡፡ሀገራችን የተጣራ ኢንተሊጅንስ በአስተማማኝ ደረጃ እንዲኖራት ማድረግ፥ እንደ መጀመሪያው

የመከላከያ መስመር ሊቆጠርላት ይችላል። “ ትንሽ ልሙትና ወዳጅ ጠላቴን አውቄ ልምጣ /ልነሳ። ” እንደሚባለው፥ በሞትና በሽረት መካከል የምትገኘው ሀገራችን ፥በዚህ አስተዛዛቢ ዘመን ፥ከልጆቿ በስተቀር የቅርብ ጎረቤትም ይሆን የሩቅ ዘመድ እንደሌላት አረጋግጣለች ። የአንድ ሀገር የውጭ ዲፕሎማሲ የሚመሠረተው፥ “ ቋሚ ወዳጅ ወይም ዘላቂ ጠላት የሚባል ነገር የለም፥ ሊኖር የሚችለው ግን ዘላቂ ጥቅም ብቻ ነው ። ” በሚል ይትበሃል ላይ መሆኑ ልንገነዘብ ይገባል። እንዲያው ለመሆኑ፥ በዚህ ተለዋዋጭ ዓለም ቋሚ ወደጅ ይኖረኛል ብሎ ሊያስብ የሚችል የትኛው ሀገር ሊሆን ይችላል ? ሁለት የዓባይ ወንዝ ተጠቃሚ ሀገሮች፥ጥቅማቸውን በበለጠ ለማስጠበቅ የሚያስቾላቸውን ዕድል ለመግኘት ለብዙ ጊዜ ሲጠባበቁ ኖረው ይኸው ዛሬ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም አሳልፎ የሚሰጥ ቡድን ስላጋጠማቸው ላሜ ወለደችልኝ ብለዋል ። ነገ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም የሚያስጠብቅ ቀናዒ ኢትዮጵያዊ ኃይል ሲመጣ ሁኔታው እንደሚለውጥ ማን በነገራቸው ? በዕርግጥም ሀገራቸውን ከጥቃት አድነው ብሔራዊ ጥቅሟን የሚያስጠብቁላት የቁርጥ ቀን ልጆቿ ብቻ እንደሆኑ ማንም ሊጠራጠር አይችልም ። ይህ ታውቆ በመጀመሪያ ደረጃ ፥ ማነኛውም ብሄራዊ ፖሊሲ ሊወጣና ሊቃኝ የሚገባው የሀገሪቱን ኅልውና ከአደጋ ለማዳን አንፃር መሆን አለበት ። ምንም ተባለ ምን፥የማነኛውም ሀገር የውጭ ፖሊሲ የሚነደፈው የዚያኑ ሀገር ብሄራዊ ደኅንነትና ዘላቂ ጥቅም ከመጠበቅ አኳያ በመሆኑ የኢሕአፓም የውጭ ፖሊሲ መመሪያ የሚቃኘው በዚህ መሠረታዊ መርኅ ላይ ነው።